ጥልቅ ተሀድሶውና የወቅቱ ይዞታ

ይነበብ ይግለጡ

ተሀድሶው በየማእዘናቱ ቀጥሎአል፤ በመላው ሀገሪቱ የለውጥ ንፋስ ይነፍሳል፡፡ ሂደቱ ብልሹ አመራሮችንና አሰራሮችን ነቅሎ በመጣል በአዳዲስ አሰራሮች የመተካት ስርነቀል እርምጃ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ተሀድሶው በህዝብ ሊታገዝ፣ ሊደገፍና ሊበረታታ ይገባዋል፡፡

ለውጥ ሁሌም በአንድ ጀምበር አይመጣም፤ ግዜና ሂደት ይጠይቃል፡፡ ቀስ በቀስ፣ ደረጃ በደረጃ ነው ለውጥ ስር እየሰደደ ሊሄድ የሚችለው፡፡ አመራሮችን ማንሳትና መለወጡ የሰው ለውጥ ሊሆን ነው የሚችለው፡፡ ትልቁና መለወጥ ያለበት መሰረታዊ ነገር አስተሳሰብን የመለወጥ ጉዳይ ነው፡፡

አለምን የለወጣት፣ የደረሰችበትም ደረጃ እንድትደርስ ያደረጋት የሰው አስተሳሰብ ነው፡፡ መሰራት ያለበትም የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ በሕብረተሰቡ ውስጥ እንዲመጣ ለማድረግ ነው፡፡ በአስተሳሰባቸው ተቸክለው እዛው የሚፍገመገሙ ዛሬም በጥንቱ እሳቤና ቀመር የሚያሰሉ ሰዎች ለለውጥ እንቅፋት እንጂ የለውጥ መሪ መሆን አይችሉም፡፡ ዛሬ ላይ ሕብረተሰቡ የደረሰበትን የእድገት ደረጃ፣ የአስተሳሰብ ምጥቀትና የእውቀት ከሂሎት የቴክኒዮሎጂውን ልቀት የተረዱ ከአካባቢያችንና ከአለም ፈጣን ለውጥ አንጻር አመለካከትና ቅኝታቸውን አስተካክለው መራመድ የሚችሉ ሰዎች ብቻ ናቸው የለውጥ ሂደት መሪ መሆን የሚችሉት፡፡

ሕብረተሰብና ሀገር የመምራት ኃላፊነት ተሸክመው ስለሀገር ሰፊ ራእይ የሌላቸው በጠባብ የአስተሳሰብ ሸለቆ ውስጥ ተጠፍንገው የሚንከላወሱ ሰዎች ሰፊ ራእይ ሰንቀው ስለሀገር ሊቆሙ አይችሉም፡፡ ጎጠኝነትና መንደርተኝነት ለዚህች ታላቅ ሀገር አያስፈልጋትም፡፡ ጠባብነትና ትምክህትም አጥፊዋ እንጂ የሚጠቅማት አይደለም፡፡ ከድህነት ለመውጣት ትልቅ ትግል እያደረገች ባለች ሀገር ዜጎችዋ መትጋት ያለባቸው በሙሉ እንደ አንድ ሰው በመቆም፤ ጸንተው በመንቀሳቀስ ድህነትን በድል አድራጊነት አሸንፎ ለመውጣት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ሂደት የሕዝብ አደራና ኃላፊነትን ተሸክመው፣ በመንግስት ቢሮ ተቀምጠው በብልሹ አሰራር ሲማግጡ የነበሩ ተሿሚዎች ይሄ ታላቅ ሕዝብ ሊሸከማቸው አይችልም፡፡

ሙሰኛውና ኪራይ ሰብሳቢው ለሕዝብ ከመስራት ይልቅ ለራሳቸው ጥቅም በሰፊው የተንቀሳቀሱ ሲሆን ሕዝቡን የመልካም አስተዳደር፣ የፍትህና ሌላም ሌላም በደል አድርሰውበታል፡፡ ታላቅ በደል ፈጽመውበታል፡፡ መንግስትም ይሄንን አምኖ ተቀብሎ ነው ችግሩን ከስሩ ለመፍታት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው፡፡

ሕዝቡ በየተሀድሶው የግምገማ መድረኩ እያጋለጠና እየመነጠረ በማውጣት እንደጥፋታቸው ክብደትና ቅለት ውሳኔ እየሰጠ በመሄድ ላይ ያለውም ራሱ ነው፡፡ የተሀድሶው መድረኮች ሰፊ፣ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በእጅጉም አሳታፊ ናቸው፡፡ በብዙ መልኩ በብዙ ሀገራዊ ጉዳዮች ሰራተኛውም ሆነ ሕዝቡ ተነግረው የማያልቁ ሀሳቦችን በግልጽና በአደባባይ እንዲንሸራሸሩ አድርጎአል፡፡

በመንግስትና በሕዝብ ወንበር ላይ ተቀምጦ ከደላላና ከሙሰኞች ጋር የጥቅም ተጋሪ በመሆን መዝረፍ፣ በፎርጅድ ስራዎች ውስጥ ተዋናይ መሆን በሕዝብ ላይ የመልካም አስተዳደርና የፍትህ በደል መፈጸም ወዘተ እንዲፈጠር ያደረጉት እነዚሁ ወገኖች ናቸው፡፡ ሙሰኝነትና ኪራይ ሰብሳቢነት ጎሳና ብሄር አይለይም፡፡ የአስተሳሰብና የአመለካከት ድህነት፣ ስግብግብነትና አልጠግብ ባይነት የቀን ጅብ መሆን የሚያመጣው ጣጣ ነው፡፡ ሙሰኞችና ኪራይ ሰብሳቢዎች ዘርፈውም ነጥቀውም በሀብት ላይ ሀብት ደራርበው ከምረውም በቃኝን አያውቁም፡፡ ይህው ቅጥና መረን የወጣ ጥቅም አጋባሽነት ባልደከሙበት የመክበር አባዜያቸው ነው ለውድቀት የሚያበቃቸው፡፡

ተሀድሶው በደቡብ ክልልም በስፋት ቀጥሎ ከርሞአል፡፡ በተሀድሶው ግምገማ 20ሺህ 173 ከፍተኛ አመራሮችን ከኃላፊነት ማንሳቱን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አስታውቀዋል፡፡ አቶ ደሴ ዳልኬ የክልሉ ምክር ቤት አራተኛ መደበኛ ጉባኤውን ሲጀምር እንደገለጹት ባለፉት ስድስት ወራት የጥልቅ ተሀድሶ መድረኮችንና የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን ለማሳካት የሚያስችል ርብርብ ተደርጎ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ 496 ሺህ 311 አመራሮች በግምገማው ሂደት እንዲያልፉ ተደርጎ 1ሺ 920 ከፍተኛ አመራሮችና 18ሺህ 253 መካከለኛ አመራሮች ከኃላፊነት እንዲነሱ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

የሕዝብ ጥያቄዎችን በመለየት በሕዝብ የተደራጀ ተሳትፎ ለመፍታት በተደረገው ጥረትም የተለያዩ እርምጃዎች መወሰዳቸው ታውቆአል፡፡ የክልሉ ርእሰ መስተዳድር ባቀረቡት ሪፖርት በሕብረተሰቡ ውስጥ የመልካም አስተዳደር ቅሬታ እየፈጠሩ ባሉ የመሬት አስተዳደር ሙያተኞችና ኃላፊዎች፣ ሕገወጥ የትምህርት ማስረጃ በተጠቀሙ፣ የተመዘበረ የመንግስትና የሕዝብ ገንዘብ ለግላቸው ባዋሉ አካላት ላይ እርምጃ መወሰዱን ማስታወቃቸውን የደቡብ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ዘግቦአል፡፡

የደቡብ ክልል ምክር ቤት ጉባኤ በስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት 18 ዳኞች እንዲነሱ ሲያደርግ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ለከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለወረዳ ፍርድ ቤቶች የ116 ዳኞችን ሹመት አጽድቋል፡፡ ምክርቤቱ የተሰጣቸውን የዳኝነት ስልጣን ለግል ጥቅም በማዋልና በስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት 18 ዳኞችን እንዲነሱ ሲያደርግ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ለከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለወረዳ ፍርድ ቤቶች የ116 ዳኞችን ሹመት አጽድቆአል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በተካሄደው ጥልቅ ተሀድሶ በኪራይ ሰብሳቢነት የተጠረጠሩ ከ3ሺህ 400 በላይ አመራሮችን በሕግ ለመጠየቅ ማስረጃ እየተሰበሰበ መሆኑን የክልሉ ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ አዲሱ አረጋ በክልሉ የተካሄደውን የመጀመሪያ ምዕራፍ ጥልቅ የተሀድሶ ጉዞ መጠናቀቅ አስመልክተው በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል፡፡ በጥልቅ ተሃድሶ ግምገማው ሕዝቡን ያማረሩና ለቅሬታ የዳረጉ ዋና ዋና ችግሮችን መለየት መቻሉን፤ የተነሱት ችግሮች ባለቤት እንዲኖራቸው ለማድረግ በተለዩ አካላት ላይ ፖለቲካዊና ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ማስረጃዎች እየተሰባሰቡ መሆናቸውን ሀላፊው ገልጸዋል፡፡

በተወሰዱ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ሁለት አመራሮች ከስራ አስፈጻሚ ወደ ማዕከላዊ ኮሚቴ እንዲሸጋሸጉ የተወሰነ ሲሆን ሶስት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መታገዳቸውን፤ ከክልል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር 4ሺህ 660 አመራሮች ከኃላፊነታቸው መነሳታቸው፤ በቀበሌ ደረጃም ከ13ሺህ 500 በላይ አመራሮች እንዲነሱ መደረጉ የተሀድሶው እርምጃ ውጤት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

አመራሮቹ የታገዱት በአቅም ማነስ፣ በኪራይ ሰብሳቢነት፣ በስነ ምግባር ጉድለትና በሌሎች ምክንያቶች መሆኑ ታውቋል፡፡ በሕግ አግባብ በተወሰዱ እርምጃዎችም ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ 946 አመራሮች በኪራይ ሰብሳቢነት ተጠርጥረው ማስረጃ እየተሰባሰበ መሆኑንና 260 የሚሆኑት በቁጥጥር ስር ውለው ክስ እንደተመሰረተባቸው ታውቆአል፡፡

በቀበሌ ደረጃ የተጠረጠሩ 2ሺህ 470 የአመራር አባላትን ለሕግ ለማቅረብ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከሰባት ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ፣ አራት ተሽከርካሪዎች፣ 40 መኖሪያ ቤቶችና ከ244ሺህ ካሬ ሜትር በላይ የከተማ መሬት በሕግ እገዳ ተጥሎባቸው ተጨማሪ ምርመራ እየተካሄደባቸው መሆኑንም ሀላፊው ገልጸዋል፡፡

በማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች የክልሉ ሕዝብ ፍላጎትና አቅርቦት ባለመጣጣሙ ከፍተኛ ቅሬታ ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን የክልሉ መንግስት ሌሎች ከመልካም አስተዳደር እጦት ጋር ተያይዘው ሲነሱ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ወደ ጥልቅ ተሃድሶ ግምገማ መግባቱ በመጠኑም ቢሆን የተገኙትን ለውጦች ለማምጣት አስችሎታል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በጥልቅ ተሃድሶው ሂደት ከማዕከላዊ ኮሚቴ እስከ ቀበሌ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች ተካተው በድምሩ ከ6 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ መሳተፉን ሀላፊው ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም ከክልሉ 20 ዞኖችና 10 የከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ 20ሺህ ሰዎች የጥልቅ ተሃድሶ ጉዞው ሂደት ላይ መወያየታቸው ታውቆአል፡፡

ሕብረተሰቡ በተለይም የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭና ተግባራት በሆኑት የመሬት አስተዳደር፣ የግዥና ኮንትራት አስተዳደርና ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ ከፍተኛ ችግር መኖሩን በውይይቱ ወቅት በሰፊው አንስቶአል፡፡የስርአቱ አደጋ የሆኑት ጠባብነት፣ አክራሪነትና ጎሰኝነት በአመለካከትና በተግባር መኖራቸውንም ሕዝቡ ገልጾአል፡፡